# የቤይጂንግ ኦሎምፒክ መታሰቢያ

## በድል ተመለሱ

ከኦሎምፒክ አገር በሰላም ደርሳችሁ፣
በድል ተመለሱ በሆታ ያግባችሁ።
ልምዱ እንዳይቀርብን በዕለት በዘመኑ፣
አዲስ ክብረ ወሰን አስመዝግባችሁ ኑ።
ቀድሞ ስለ እናንተ ዓለም ያወራውን፣
ቤይጂንግ አይታ ትመን የተነገረውን።

ዛሬም በልጆችሽ የድል መታሰቢያ፣
በዓለም እንዲደረግ አንቺ እናት ኢትዮጵያ፣
መርቀሽ ላኪያቸው «በድል ግቡ» ብለሽ፣
አረንጓዴ ቢጫ ቀይ ባንዲራ አልብሰሽ።
ወርቅ አጥልቆ መምጣት ባንዲራ አስከብሮ፣
እንደ ቀድሞው ዘመን ይሆናል ዘንድሮ።

*ኃይሌ ቀነኒሳ ስለሺ* እና *ዘምዘም*፣
*ገለቴ ደሪባ ጉዲሳ መስከረም*፣
*ዓሊ ናሆም ዴማ ኢብራሂም መሠረት*፣
*ድሬ ሮባ ጌጤ ሶፍያ መስታወት*፣
*መቅደስ ውዴ ጋሻው ፀጋዬ ጥሩነሽ*፣
*ሙሉጌታ አብርሃም መኮንን ብዙነሽ*፣
በጣም ተጠናክረው በኃይል በወኔ፣
*መሰለች ደረሰ ያዕቆብ ብርሃኔ*፣
ድል እየታያቸው የማይቀር ሽልማት፣
*ታሪኩ እጅጋየሁ በላይነሽ* በብቃት፣

ሰንደቅ ዓላማችን ከፍ ብሎ እንዲታይ፣
እጅግ ተዘጋጅተው ከመቼውም በላይ፣
ሊመጡ ነውና ጀግኖቹ በኅብረት፣
ሜዳሊያውን ቤይጂንግ ስም አስቀርጪበት።
ኢትዮጵያ በይና ማኅተም አትሚበት፣
አፍሮ አይመለስም ወርቅ የለመደ አንገት።

ኦሎምፒክ ጀመረሽ ከአሁኑ መርበትበት፣
የአበበ ስም አለ መዝገቡ ሲከፈት።
የድል ቃል-ኪዳን ነው በምድር ያተመበት፣
ሮም በባዶ እግሩ ዱካው ያረፈበት።

ማራቶን ሲታሰብ ማራቶን ሲታለም፣
ኢትዮጵያ የሚባል ስም ትዝ ይለዋል ዓለም።
ድል ያ ደርጋል ብሎ ዓለም ያልጠበቀው፣
በምናልባት መዝገብ ኦሎምፒክ ያልጻፈው፣
የአፍሪካ ምልክት የኢትዮጵያ ኩራት፣
በሮም ታሪክ ሠርቶ በቃ ለሽልማት።
በወርቅ መዝገብ ላይ በወርቃማ ቀለም፣
ስሙ ተመዝግቧል ላይጠፋ ዘላለም።

Ethiopia Will Prevail!

ለትዝታ እንዲሆን ኢትዮጵያን ካስጠሩት፣
ሰንደቅ ዓለማዋን በዓለም ካስከበሩት፣
ጥቂቱን እንጥቀስ ለናሙናው ያህል፣
ሁሉንም ዘርዝረን መግለጽ እንኳን ባንችል።

ኦሎምፒክ ሲወሳ ሲነገር ሲዘከር፣
ዓለም ትዝ ይለዋል ጀግናው ምሩፅ ይፍጠር።
አንዴ ካመለጠ ምሩፅ ማን ሊይዘው፣
በሃሳብ እንጂ በአካል አይደርስበትም ሰው።
ሞስኮ መስክራከች ስላየችው ነገር፣
ወርቅ ይዞ መግባቱን ሻምበል ምሩፅ ይፍጠር።

ኢትዮጵያን ወክለህ የዛሬ አራት ዓመት፣
የሲድኒው አንበሳ ብቅ እንድትል ድንገት።
ትጠብቅ'ካለች እጆቿን ዘርግታ፣
ኦሎሞፒክ ለድልህ ወርቋን አዘጋጅታ።
ወርቁን ስትሸለም ተጎናጽፈህ ዝና፣
ሚሊዮን ይባላል በዓለም እንደገና።
ኢትዮጵያ ንገሪው ለሚሊዮን ወልዴ፣
ኦሎምፒክ ድል ማድረግ እንዳይበቃው በአንዴ።

እማኝ ምስክር ነው የሮጠበት ምድር፣
በድል እየገባ ስላገኘው ክብር።
ለንዳፍታ አይረሳም የፈጸመው ተአምር፣
የኢትዮጵያ ክቡር ልጅ ያ መሐመድ ከድር።

ኦሎምፒክ ሦስት ጊዜ ላሸነፋት ጀግኖች፣
ወርቅ ስትሰጥ ኖራ ለኢትዮጵያ ልጆች፣
በክብር ላይ ክብር እየተዘገበ፣
አንዱን ማሞ ወልዴ ሁለቱን አበበ፣
ገንዘባቸው ሆኖ ተሸልሞ መምጣት፣
ባንዲራ አውለብልቦ ኢትዮጵያን ማስጠራት፣
በሮም በቶክዮ በሜክሲኮ አገራት፣
ድል የኢትዮጵያ ነበር ለአስራ ሁለት ዓመታት።

ማራቶን ድል ማድረግ በኦሎምፒክ መንደር፣
በአበበ በማሞ ተወስኖ ነበር።
ለረጅም ዓመታት ከእነርሱ በኋላ፣
የማራቶን ክብር ነበረ ለሌላ።
በሮም በቶክዮ ሜክሲኮ እንደታየው፣
አሰፋ መዝገቡ ሲድኒ ላይ መለሰው።

<ኢካቦድ> አይባል ክብር ከእኛ አልራቀም፣
ዛሬም ወደፊትም ታዋቂ ነን በዓለም።

እንኳንስ ኢትዮጵያ የተወለድሽባት፣
አፍሪካ ኮርታለች በእስፔኑ ሽልማት።
አረንጓዴ ቢጫ ቀይ ባንዲራ ልብሱ፣
እንደ አንቺ ዓይነት ጀግና ክብር ነው ትራሱ።
የባርሴሎናን ድል በሲድኒ የደገምሽ፥
የኢትዮጵያ ኩራት ደራርቱ ቱሉ ነሽ።
በአንቺ እግር የተተኩ አንቺን ያዩ ናቸው፥
ዛሬ በዓለም መዝገብ ታሪክ የጻፉቸው።

አንተም እንደ አበበ አንተም እንደ ማሞ፡
ማራቶን ድል አርገህ በላይነህ ዲንሳሞ፡
አዲስ ክብረ ወሰን በዓለም አስመዝግበህ፡
ክብርህን ለዓመታት ያቆየህ አንተ ነህ።
        በአበበ ቢቂላ እግር የተተካሽ፡
        በሴቶች ማራቶን ኢትዮጵያን ያስጠራሽ፡
        የመጀመሪያ ሴት በኢትዮጵያ በአፍሪካ፡
        የማራቶን ጀግና ፋጡማ ነሽ ለካ።
በመሰናክል የሯጮች አውራ፡
ስምህ ክቡር ነው እሸቱ ቱራ።
        ትዝ የምትለን ሲመሽ ሲነጋ በየሰዓቱ፡
        የድል ባለቤት የኢትዮጵያ ኩራት ቶሎሳ ቆቱ።
«ሾላ» የሚባል ስም ወገን የሰጠህ፡
ሥራህ ሕያው ነው ትታሰባለህ።
        ለኢትዮጵያ ሕዝብ ክብሩ ኩራቱ፡
        ትልቅ ታላቅ ሰው ዋሚ ቢራቱ።
ድል ያበሰራችሁ ለአንዲት ውድ ኢትዮጵያ፡
ብርሃኑ እና አዲስ እንዲሁም ሉቺያ፡
        በዕልፍ ይቆጠራሉ ችዬም አልገልጻቸው፡
        ሌሎቹን ሯጮች ታሪክ ይቁጠራቸው።
        ምድር ምስክር ነች ለጀግንነታቸው፡
        ሜዳል ለጠገበው ለአንገት ደረታቸው።
        የታሪክ መዝገብ በወርቅ የጻፋቸው፡
        ከአእምሮ ተቀርፀው ልብ ያስቀመጣቸው፡
        እገሌ እና እገሌ ኧረ እነማን ናቸው፡
        አንድ ወይስ አንድ ሺ ስንት ነው ቁጥራቸው?
የኢትዮጵያ ልጆች እንግዲህ አደራ፡
የቤይጂንግ ኦሎምፒክ የእናንተን ስም ይጥራ።
አዲስ ክብረ-ወሰን በማራቶን ያለህ፡
ዕልል ይበል ምድሩ ኃይሌ በድል ገብተህ።
        ወርቅ አርገህ ተመለስ በክብር ስለሺ፡
        ለአንተ ይሁን ድሉ የዘንድሮ አሥር ሺ።
በአሥር በአምስት ሺ በሁለት ውድድር፡
ድል አርጋችሁ ግቡ በክብር ላይ ክብር፡
        ኦሎምፒክ ጉድ ይበል ዓለም ያስተጋባ፡
        ሁለቱን ወርቅ ይዘሽ ጥሩነሽ ዲባባ።
ዛሬም ታሪክ ሠርተህ ስምህን አስነሣ፡
የዓለም ፈጣን ሯጭ ጀግናው ቀነኒሳ።

        ሁላችሁ ጠንክሩ በርቱ አምላክ ይርዳችሁ፡
        እስራ ምእት ዓመት ለተአምር ያብቃችሁ።
        ተከታተሉና ከአንድ እስከ ሦስት ውጡ፡
        ወርቁንም ብሩንም ነሐሱንም አምጡ።

ወስብሐት ለእግዚአብሔር!!

አብርሃም ሰሎሞን
ሚኒያፖሊስ ሚኒሶታ (አሜሪካ)
Abraham.Solomon@yahoo.com

ሐምሌ ፴/፳፻ ዓ.ም